ከ ጎቦ ውቃው

## እውነትም ወለፈንዲ!

ይብላኝ ላንተ. . .
. . . ለፈሪ ለበጭባጫ
ቡኮ መሳይ መርግጫ
መሰረት ውሉን የረሳ
በበላበት የሚያገሳ
ኑሮው ሁሉ እንደ ሰሳ፤
የሰፈረበት ዉቃቢው
የእውቀት ድህነቱ ገኖበት
እንደ ሰማይ ዙር መቀነት
“ቀስተ-ደመና” የሆነበት፤
ግን ከተገፋው የመጣ
በበላበት የሚንጣጣ
ሃሳቡ ሁሉ ጎባጣ
የቦለቲካ ለማጣ፤
ለማህተብ የመሞትን. . .
የኢአባውን ጠበል ልርጨው?
ወይ የአገር አውራነቱን
የሻውልን ጠበል ልርጨው?
የባንድነቱን ኩፍኝ. . .
ሰንኮፉ ተንቅሎ. . .
ከዘር-ማንዝሩ እንዲምረው
አንዳን
አልያስ! አልያስ! ክፍቴ
የአንተ ዱበርቲ-አተቴ
የመዋ-ፅጌ ዙር ብቴ
ጣሪያ ክዳኑ ይነቀላል

ጉድ ገበናው ይጋለጣል
. . . ሳይቀጣህም ላይመለስ
አባ እምብየው ጨክኖአል።
በኛ፡ቋንቋ ተነጋግሮ
ማደናገር ቀረ ድሮ
የባንድነቱ ውርዴ
ካንፉአቀቀው በዳዴ
የነውር፤የባህል፤ድህነት
የስነ-ምግባር ዳፍንት
በአስራአንደኛው ሰዓት
ሊሄድ ከዳዳው የሁአሊት
አንተን አያርገኝ ክፍቴ. . .
የመንጎሉ ስለት ካፎቱ አይገባም
አንተን ሳይቀጣ ሳያርም
ለአንዴም ለዘለ-ዓለም
. . . ዓለም፤
ከረካ በራሱ ቅርሻ
ብስናውን ልያጣጥም ካሻ
መጨበጪያው ከጠፋበት. . .
. . . መቅደስ እንደገባች ውሻ፤
ኩስ እንደነካት እንጨት
ዙሪያው ገደል ካልሆነበት
የመንጎሉ ስለት ካፎቱ አይገባም
አንተን ሳይቀጣ ሳያርም
ለአንዴም ለዘለ-ዓለም
. . . ዓለም፤